የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

06/09/2012

ቁጥር / Ref: ፕ-ዐ፩-ር/1.1.18/7924/ሬ

ቀን/Date: ግንቦት 0 9 2012

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ለሀረማያ ዩኒቨርስቲ
ለሀዋሳ ዩኒቨርስቲ
ለመቀሌ ዩኒቨርስቲ
ለመደወላቡ ዩኒቨርስቲ
ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ
ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ
ለሰመራ ዩኒቨርስቲ
ለአክሱም ዩኒቨርስቲ
ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ
ለዲላ ዩኒቨርስቲ
ለደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ
ለራያ ዩኒቨርስቲ
ለመቅደላ አምባ ዩኒቨርስቲ
ለጂንካ ዩኒቨርሲቲ
ለወሊጋ ዩኒቨርስቲ
ለወሎ ዩኒቨርስቲ
ለደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ
ለደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ
ለድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ
ለባህርዳር ዩኒቨርስቲ
ለጎንደር ዩኒቨርስቲ
ለጅማ ዩኒቨርስቲ
ለጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ
ለአምቦ ዩኒቨርስቲ
ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ
ለአዲግራት ዩኒቨርስቲ
ለእንጅባራ ዩኒቨርስቲ
ለቦንጋ ዩኒቨርስቲ
ለደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ
ለአዳማ ሳይ/ቴክ/ዩኒቨርሲቲ
ለአዲስ አበባ ሳይ/ቴክ/ዩኒቨርስቲ
ለወልድያ ዩኒቨርስቲ
ለወልቂጤ ዩኒቨርስቲ
ለዋቸሞ ዩኒቨርስቲ
ለመቱ ዩኒቨርስቲ
ለቡሌሆራ ዩኒቨርስቲ
ለአሶሳ ዩኒቨርስቲ
ለጋምቤላ ዩኒቨርስቲ
ለኮተቤ ሚትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ
ለሰላሌ ዩኒቨርሲቲ
ለኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርስቲ
ለደባርቅ ዩኒቨርስቲ
ለወራቤ ዩኒቨርስቲ
ለቀብሪ ደሀር ዩኒቨርሲቲ

ባሉበት

ጉዳዩ፡- የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበት መመሪያን

ስለመላክ

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት አዋጅን ተከትለው መውጣት ያለባቸውን ደንቦችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ላይ ሲገኝ በቅርቡም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 456/2012 አጸድቆ ስራ ላይ እንዲውል ማድረጉ ያታወቃል፡፡

በዚሁ መሰረት ደንቡን ተከትሎ "የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበትን መመሪያ ቁጥር 04/2012" የፀደቀ በመሆኑ መመሪያው ሥራ ላይ እንዲውል ....ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሂሩት ወ/ማርያም ተከተል (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

ግልባጭ
- ለሳይ/ከፍ/ትም/ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለሳይ/ከፍ/ትም/ሚኒስትር ዴኤታዎች ጽ/ቤት/3/
- ለከፍ/ትም/አስ/ሪፎ/ዳሬ/ጄነራል
- ለከፍ/ትም/ተማ/ጉዳ/ዳይሬክቶሬት

ሳ/ከ/ት/ሚ
- ለኢ.ፌዲሪ የገንዘብ ሚኒስቴር

አዲስ አበባ

# የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች

# የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ

# መመሪያ ቁጥር 04/2012

ሳ/ከ/ት ሚኒስቴር

ታህሳስ/2012 ዓም

# የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች
# የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ

አገሪቱ ለጀመረችው ፈጣን ኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገትና ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ከፍተኛ ትምህርት ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት በመረዳት፣

ከፍተኛ ትምህርት ውድና ከፍተኛ የሆነ መዋእለ ነዋይ የሚጠይቅ በመሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሂደት በራሳቸው ኃብት የሚያመነጩበትን ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ፣

የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የካፒታል አመዳደብና የገቢ አጠቃቀምን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣

ይህ መመሪያ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል

1. **አውጭው ባለስልጣን**

   የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀጽ 11 / 1 / መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ መመሪያ "የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበት የአሰራር ስርዓት ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ትርጓሜ

1. "ከፍተኛ ትምህርት" ማለት በስነ-ጥበብ፣ በማህበራዊ ሳይንስ እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ የድግሪ ፕሮግራሞች የሚሰጥ ትምህርት ነው፤
2. **"የመንግስት ተቋም"** ማለት እንደ አግባብነቱ በጀቱ በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት የሚመደብለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤
3. "የገቢ ማስገኛ ድርጅት" ማለት አንድ የመንግስት ተቋም በደንብ ቁጥር 456/2012 መሠረት የሚያቋቁመውና በዚህ መመሪያ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የሚያስተዳድረው የንግድ ድርጅት ነው፡፡
4. "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 ነው፡፡
5. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
6. "ደንብ" ማለት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 ነው፡፡
7. ሌሎች በመመሪያው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ እና በደንቡ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

1. የገቢ ማስገኛ ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ቦታ ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላል፡፡
2. ሆኖም ግን ዋናው መስሪያ ቤት ላይም ሆነ በቅርንጫፍ የሚቋቋሙት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የዩኒቨርስቲውን ተልዕኮ መሰረት ያደረጉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

5. **ዓላማ**

የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ የተቋቋመበት ዓላማ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር ተያያዥ በሆነ መልኩ ገቢ ሊያገኙ የሚችሉባቸውን አገልግሎቶች በመስጠት የውስጥ ገቢ አቅማቸውን ማሳደግ፡፡
2. ከውስጥ ገቢ የሚገኘውን ገቢ ለተልዕኮና ለዓላማ ማስፈፀሚያ እንዲውል በማድረግ ተልዕኳቸውን በላቀ ሁኔታ መፈፀም ማስቻል፡፡
3. ዓላማውን ከግብ ማድረስ የሚያስችሉ ከተሰጣቸው ተልዕኮ አንፃር ሌሎች ስራዎችን መስራት፡፡

6. **የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ አቋምና አመራር**

1. በደንብ ቁጥር 456/2012 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ስራ አስኪያጅ በቦርድ ስብሰባዎች አስረጂ ሆኖ የሚቀርበው የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡
2. በዩኒቨርስቲው የተቀጠሩ ባለሙያዎች በገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ውስጥ ተቀጣሪ ሆነው ማገልገል አይችሉም፡፡ ሆኖም ግን መደበኛ ስራቸውን

ለቀው በገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ውስጥ ተወዳድረው መቀጠር ይችላሉ፡፡

3. የገቢ ማስገቢኛ ድርጅቱ የሚተዳደርበትን የውስጥ የአሰራር ዝርዝር መመሪያ ከዚህ መመሪያ ጋር በተጣጣመ መልኩ የዩኒቨርስቲው ቦርድ ያወጣል፡፡

## 7. የካፒታል

1. ለገቢ ማስገኛ ድርጅቱን ካፒታል የዩኒቨርስቲው ቦርድ በሚቀርብለት የድርጅት ማቋቋሚያ መሰረት የተከፈለና የተፈቀደ ካፒታል መጠኑን ይወስናል፡፡

2. የገቢ ማስገኛ ድርጅት የሌላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያቋቁሟቸው የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የመነሻ ካፒታል ተቋማቱ ከሚያገኙት የውስጥ ገቢ በአምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የሚከፈል ይሆናል፡፡

3. በሥራ ላይ ያሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች ካፒታላቸው በባለሙያዎች በትክክል ተገምቶና በኦዲተር ተረጋግጦ በዚህ ደንብ መሰረት እንደገና የሚቋቋሙ ይሆናል፡፡

## 8. የገቢ አጠቃቀም

1. የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ በየዓመቱ የሚያገኘውን የተጣራ ትርፍ ከተቋቋመበት ግዜ አንስቶ እስከ አምስት አመት ወይም የተፈቀደውን ካፒታል ጣራ እስከሚደርስ ድረስ 60% ለገቢ ማስገኛ ለካፒታል ማሳደጊያ 40% ለዩኒቨርስቲው ተልዕኮና ዓላማ ማስፈፀሚያ በጀት ድጎማ እንዲውል ያደርጋል፡፡

2. በዚሁ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ከአምስት አመት በኋላ ወይም የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ የተፈቀደውን ካፒታል ካሟላ በየዓመቱ የሚያገኘውን የተጣራ ትርፍ 20% ለካፒታል በጀት 80% ለዩኒቨርስቲው ተልዕኮና ዓላማ ማስፈፀሚያ በጀት ድጎማ እንዲውል ያደርጋል።

3. ሆኖም ከተጣራ ትርፍ ለዩኒቨርስቲው ተልዕኮና ዓላማ ማስፈፀሚያ የሚበጀተው በጀት በመንግሥት ተመን የወጣላቸውን እንቅስቃሴዎች ለመደጎሚያ አይውልም።

## 9. ስለ ሂሳብ መዛግብት

1. የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ IFRS ተከትሎ የተሟሉና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የገቢ ማስገኛ ድርጅቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው የውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ያስመረምራል።

## 10. ልዩ ድንጋጌ

የመመሪያው ተግባራዊ ፋይዳ በተጨባጭ መረጃ ለመገምገምና በተቋም ደረጃም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ አስፈላጊ የአቅጣጫ ማሻሻያዎችን ለማድረግ እንዲቻል ተቋሙ ተገቢውን መረጃ ለቦርዱና ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

## 11. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሚኒስትሩ ሊሻሻል ይችላል

## 12. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

መመሪያው ጸደቆ ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ሂሩት ወ/ማርያም (ፕሮፌሰር)

የኢፌዲሪ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር